**General Relief Society Meeting**
**September 24, 2011**

# ከገባሽው ቃል ኪዳን ጋር ምተጣበቂ

በባርብራ ቶምሰን

የሴቶች መረዳጃ ማህበር አመራር ሁለተኛ አማካሪ

“ልብሽን አንሺ እናምተደሰቺ፣ እና ከገባሽውቃል ኪዳን ጋርምተጣበቂ። ”[1] ይህን የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅስት ደስታ ሳይሰማኝ ማንበብ አልችልም። ከሰማይ አባቴ ጋር ከገባኋቸውቃል ኪዳኖች ጋር ለመጣበቅ በምጥርበት ጊዜ በህይወቴ ክፍል ለነበሩት የተስፋ ቃላት እና በረከቶች ሳስብ ልቤ ትደሰታለች።

ወላጆቼ ስለሞቱ፣ ቤታቸውን ማጽዳትና ለመሸጥ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነበር። ወንድሞቼ እና እህቶቼና እኔ የወላጆቻችንን ቤት ስናጸዳና ስናስተካክል፣ የቤተሰብ ታሪክን እና ሌሎች አስፈላጊ ወቀረቶችን አገኘን። የወላጆቼንና የአያቶቼን ማስታወሻ ወረቀቶችን እና የፔትሪያርክ በረከቶቻቸውን ማንበብ ያስደንቅ ነበር። እነርሱ ስለገቡትና ስለጠበቁት ቃል ኪዳን እንዳስታውስም አደረጉኝ።

ሴቷ አያቴ ኤለን ሀንክስ ራይመር በ 1912 ዓ.ም የፓትሪያርክ በረከቷን ስትቀበል ወጣት እናት ነበረች። በረከቷን ሳነብ እነዚህ ቃላት በአእምሮዬ ላይ ቀሩ፥ “ከአለም መፈጠር በፊት የተመረጥሽ ፣ እና በዚህ ቀን ለመምጣት የመረጥሽ ምርጥ መንፈስ ነሽ …። ምስክርሽ ይጎላል እናም ለመመስከርም ትችያለሽ …። አጥፊውአንቺን ለማጥፋት ፈልጓል፣ ነገር ግን ከአምላክሽ ጋር ከተጣበቅሽ፣ [አጥፊው] ሊጎዳሽ ሀይል አይኖረውም። በታማኝነትሽ ታላቅ ሀይል ይኖርሻል እናም በጻድቅነትሽም አጥፊው ከፊትሽ ይሸሻል። …የፍርሀትና ፈተናዎች ጊዜ ሲመጡብሽ፣ ለጸሎት በድብቅ ቦታህ ከሄድሽ፣ ልብሽ ይፅናናል እናም መደናቀፊያዎችም ይወገዳሉ። ”[2]

አያቴ ቃል ኪዳኗን ካከበረች እና ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ ከሆነች፣ ሰይጣን ምንም ሀይል በእርሷ ላይ አይኖረውም። በፈተናዎቿም ምንም ትፅናናለች እናም ትረዳለች። እነዚህ ቃል ኪዳኖች በህይወቷ ተሟልተውነበር።

ዛሬ (1) ከቃል ኪዳኖች ጋር የመጣበቅ አስፈላጊነትን እና (2) ቃል ኪዳኖቻችንን በማክበር ስለሚመጣውደስታ እና ጥበቃ ላልጋግራችሁ እፈልጋለሁ።

የምጠቀምባቸውአንዳንድ ምሳሌዎች የሚመጡት Daughters in My Kingdom: The History and Work of Relief Society ከሚባለ መፅሐፍ ነው። ይህ መፅሐፍ ቃል ኪዳንን በማክበር ታላቅ ደስታን ባገኙ ሴቶች ምሳሌ የተሞላ ነው።

## ከቃል ኪዳኖች ጋር የመጣበቅ አስፈላጊነት

የመፅሐፍ ቅዱስ መግለጫውስጥ እንደማነበው፣ ቃል ኪዳን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚገባ ስምምነት ነው። “እግዚአብሔር በመልካም ፍላጎቱ የስምምነትን ጊዜ ይወስናል፣ ሰውም ይቀበላል። …ወንጌሉ የተመሰረተውመሰረታዊ መመሪያዎች እና ስነስርዓቶችን ተቀባዩ የሚቀበለውእርሱን ቃል ኪዳን በማስገባትና ይህን እንዲያከብር ታላቅ ሀላፊነት በመስጠት ነው። ”[3] ከቃል ኪዳኖች ጋር ተጣበቁ ማለት በፅኑ እና በቅርብ ያዙ ማለት ነው። [4]
በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ከእግዚአብሔጋር ቃል ኪዳን ስለገቡ ሰዎች እንማራለን። ፡ እነዚህን ቃል ኪዳኖች ለማክበር ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ

እግዚአብሔር መመሪያዎች ሰጥቷል፣ እና ከእዚያም እነዚህ ቃል ኪዳኖች ሲከበሩ፣ ቃል የተገቡበት በረከቶች ይከተላሉ።

ለምሳሌ፣ በጥምቀት ስነስርዓት በኩል ከሰማይ አባታችን ጋር ቃል ኪዳን እንገባለን። በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፣ ለኃጢያቶቻችን ንስሀ በመግባት፣ እና የክርስቶስን ስም በላያችን ላይ ለመውሰድ ፈቃደኞች በመሆን እራሳችንን ለጥምቀት እናዘጋጃለን። “ቀላል እንዲሆኑ፣ የእርስ በራስን ሸክም ለመሸከም” ቃል እንገባለን። ከሚያለቅሱት ጋር ለማልቀስ እና መፅናናት የሚያስፈልጋቸውን በማፅናናት ይህን እናሳያለን።[5]

በቅዱስ ቤተመቅደሶች ውስጥ ሌሎች ስነስርዓቶች ይሰጣሉ እናም ሌሎች ቃል ኪዳኖች ይገባሉ። በዳግም መመለሱ የመጀመሪያ ቀናት፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ቃል የተገባበት የቤተመቅደስ በረከትን ቅዱሳን እንዲያገኙጉጉት ነበረው። ጌታም እንዲህ አለ፣ “ስነስርዓቶቼን ለህዝቦቼ በዚህ ውስጥ እንድገልፅ ዘንድ፣ ይህም ቤት በስሜ ይሰራ።”[6]

“ጌታ የሴቶች መረዳጃ ማህበርን ያደራጀበት አንዱ አላማ በቤተመቅደስ ውስጥ ለሚገኙት የክህነት ስልጣን ስነስርዓቶች እና ቃል ኪዳኖች ሴት ልጆቹን ለማዘጋጀት ነው። በናቩ ያሉት እህቶች የቤተመቅደሱን መፈጸም በጉጉት ጠበቁ፣ ምክንያቱም ነቢዩ አሴፍ ስሚዝ መርችይ ፊልዲንግ ቶምሰንን ቃል እንደገባላት የመንፈስ ስጦታው “ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሀን ‘እንደሚያስወጣቸው’ በማወቃቸው ነው።”[7]

“የናቩ ቤተመቅደስ ከተመረቀ በኋላ፣ ወደ ሶልት ሌክ ሸለቆ ጉዞአቸውን ከመጀመራቸው በፊት የመንፈስ ስጦታዎችን እና የመተሳሰር ስነስርዓቶችን ለመቀበል 5ሺህ ቅዱሳን ተሰበሰቡ።[8] ፕሬዘደንት ብሪገም ያንገና ብዙ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች እንዲሁም የቤተመቅደስ ሰራተኞች በቀንም ይሁን በምሽት ይህ አስፈላጊ ስራ ለቅዱሳን እንዲከናወን ጊዜአቸውን አሳልፈውሰጥተዋል።

ቃል ኪዳኖቻችን በመልካም ጊዜ ይሁን በመጥፎር ጊዜዎች ይደግፉናል። ፕሬዘደንት ፓከር እንድናስታውስ እንዳደረጉን፣ “እኛ የቃል ኪዳን ህዝቦች ነን። በምድር ላይ ላለው የእግዚአብሔር መንግስት ጥቅም ያለንን ጊዜ ገንዘብ እና ችሎታ ለመስጠት ቃል ኪዳን ገብተናል። በሌላ አባባልም፣ ጥሩ ለማድረግ ቃል ገብተናል። የቃል ኪዳን ህዝቦች ነን፣ እናም ቤተመቅደስ የቃል ኪዳናችን ዋና ክፍል ነው። ይህም የቃል ኪዳን ምንጭ ነው።”[9]

ቅዱሳት መጻህፍትም እንድናስታውስ እንደሚያደርጉት፣ “ይህም ቃል ኪዳናችን ይሆናል፣ በጌታ ስርዓቶች ሁሉ እንሄዳለን።”[10]

በገባናቸው ቃል ኪዳኖች በመጣበቅ የምንቀበላቸው በረከቶች ታላቅ ናቸው።

**ደስታ እና መጠበቅ ቃል ኪዳኖቻችንን በማክበር ይመጣሉ**

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የንጉስ ቢንያምን ስብከት እናነባለን። ህዝቦቹን ስለኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወደ ምድር እንደሚመጣና ብዙ አይነት ስቃዮችን እንደሚሰቃይ አስተማረ። ክርስቶስ ለሰውዘር ኃጢያቶች ክፍያ እንደሚያደርግ እና ሰውደህንነትን ለማግኘት የሚችልበት ስም የእርሱ ስም ብቻ እንደሆነም አስተምሯል።[11]

እነዚህን አስደናቂ ትምህርቶችን ከሰሙበኋላ፣ ህዝቡ ትሁት ሆኑ እናም በልባቸውበሙሉ ከኃጢያት ነጻ ለመሆንና ለመጸዳት ፈለጉ። ንስሀ ገቡ እናም በኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት ተናዘዙ።[12] ከእግዚአብሔር ጋር ትእዛዛቱን እንደሚያከብሩ ቃል ኪዳን ገቡ።

“እነዚህን ቃላት ከተናገሩ በኋላ የጌታ መንፈስ በእነርሱ ላይ መጣ፤ እና ንጉስ ቢንያም በተናገረው ቃላት መሰረት በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው ታላቅ እምነት የተነሳ፣ ለኃጢአታቸውም ስርየትን በመቀበል፣ እናም የህሊና ሰላምም በማግኘት በደስታ ተሞልተው ነበር።”[13]

በታማኝነት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በማክበር እና ወንጌሉን ከሌሎች ጋር በመካፈል የሚመጣው ደስታ ሌላ ምሳሌ የሚታየው አሞን ባደረገው ነበር። አሞንና ወንድሞቹ ብዙ ሺህ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ለመርዳት መሳሪያዎች ነበሩ። ብዙ ሰዎች ሲጠመቁና ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳኖችን ሲገቡ አሞን ከተናገራቸው ቃላት አንዳንዶቹ እነዚህ ናቸው።

“ለደስታችን እንዴት ታላቅ ምክንያት አለን።”[14]

“ደስታዬ ሙሉ ነው፣ አዎን፣ ልቤ በደስታ ይሞላል፣ እናም በአምላኬ ሐሴት አደርጋለሁ።”[15]

“ከተሰማኝ ጥቂቱን ለመናገር አልችልም።”[16]

“እንደእኛ ለመደሰት ታላቅ ምክንያት ያላቸው ሰዎች በጭራሽ የሉም።”[17]

ቅዱስ ቃል ኪዳኖችን መግባት እና መጠበቅ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር እንዲሆን ያስችለናል። “ይህም ነፍሳችሁን በደስታ የሚሞላው” መንፈስ ነው።[18]

ሁለተኛው የአለም ጦርነት በአለም ውስጥ ብዙ ሰዎች እንዲሰቃዩ አድርጓል። በገርመን ያሉት ቅዱሳን ብዙ ፈተናዎች ነበራቸው። በስቱትጋርት ጀርመን ትኖር የነበረች ታማኝ የሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዘደንት እህት መሪያ ስፓይደል ነበረች። ስለፈተናቸው እንዲህ አለች፣ “በጌታ የነበረን እምነት እናም ስለቤተክርስቲያኑ የነበረን

ምስክራችን የጥንካሬአችን መንጭ ነበር። …የፅዮን ዘፈኖችን በደስታ ዘፈንን እናም እምነታችንን በጌታ ላይ ጣልን። ሁሉንም ነገሮች መልካም ያደርጋልና። ”19

እንደገና፣ አባላት ቃል ኪዳኖቻቸውን ሲያከብሩ፣ በታላቅ ፈተናዎችም ጊዜ ደስታ ይሰማቸዋል።

ሳራ ርች ቅዱሳን ከናቩ በግድ ከመውጣታቸው በፊት በቤተመቅደስ ውስጥ ለማገልገል የተጠራች ጻድቅ ሴት ነበረች። ስለ ቤተመቅደስ ቃል ኪዳኖች በረከቶች ቃላቶቿ እንዲህ ነበሩ፥ “በሀዘኖች መካከል ደስታ እና መፅናናት የሰጡንና በማይታወቀው ጉዞአችን እንደሚመራንና እንደሚደግፈን በማወቅ በእግዚአብሔር እምነት እንዲኖረን ያደረጉን በጌታ ቤት የተቀበልናቸው በረከቶች ብዙ ነበሩ። ”20

በፊት የከርትላንድ ቤተመቅደስን ቅዱሳኖች ገንብተው ነበር፣ እናም ብዙዎቹም በመመረቁ ተሳተፉ። ከተመረቀ በኋላ፣ ቤተመቅደሱ በጌታ ተቀባይ ሆነ ።፡ ጌታም እንዲህ አላቸው፣ “በህዝቦቼ ራሶች ላይ በሚፈሱት በረከቶች በታላቅ ይደሰታሉ። ”21

በምድር ላይ ተጨማሪ ቤተመቅደሶች ሲገነቡ፣ በአባላት ህይወቶች ላይ የሚመጡትን በረከቶች ለመመልከት ችያለሁ። በ 2008 ዓ.ም ወደ Freiberg, Germany የ ቤተመቅደስ ስነስርዓቶችን ለመቀበል ስለሄዱበት ጊዜ ስለነገሩኝ የዩክሬይን ባልና ሚስት ደስታ ምስክር ለመሆን ችዬ ነበር። ወደ ቤተመቅደሱ ለመድረስ በአውቶቡስ ለ 27 ሰዓት መጓዝ ነበረባቸው እናም በየጊዜው ለመሄድ አይችሉም ነበር። የ ኪየቭ ዩክሬን ቤተመቅደስ በቅርብ እንደሚመረቅ እና ወደዚያ ለመሄድ እንደሚችሉ በማወቃቸው በጣም ተደስተው ነበር። አሁን ያም ቤተመቅደስ ክፍት ነው፣ እናም ብዙ ሺህዎችም በረከቶችን እየተደሰቱባቸው ናቸው።

የአያቴን የግል ታሪክ በማንበብ በቃል ኪዳኖቿ ስለነበራት ደስታም ተምሬ ነበር። ወደ ቤተመቅደስ መሄድንና ለሞቱት ብዙ ሺሆች ስነስርዓቶችን ማከናወን ትወድ ነበር። ይህም የህይወቷ አላማ ነበር። በማንታይ ዩታ ቤተመቅደስ ለ 20 አመት አገለገለች። ልጆቿን ለማሳደግ እና በቤተመቅደስ ውስጥ ስራቸውን በመፈጸም ሌሎችን ለማገልገል ብዙ አስደናቂ ፍወሳ እንዳገኘች ጽፋለች። እንደ ልጅ ልጆቿ፣ ስለ አያታችን ራይመር ምንም የምናውቀው ቢኖር ቃል ኪዳኗን ያከበረች እና እኛም እንደ እርሷ እንድናደርግ የፈለገች ጻድቅ ሴት እንደነበረች ነው። ከሞትን በኋላ ሰዎች የተውነ ውን ሲመለከቱ፣ ቃል ኪዳኖቻችንን እንዳከበርን የሚያሳዩ ምልክቶችን ያገኛሉ።

ውድ ነቢያችን፣ ፕሬዘደንት ሞምሰን፣ ባለፈው አጠቃላይ ጉባኤ እንደነገሩን፥ “እናንተ እና እኔ ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ቤት ስንሄድ፣ በውስጡ የምንሰራውን ቃል ኪዳን ስናስታውስ፣ እያንዳንዱን ፈተና ለመቋቋም እና እያንዳንዱን ፈተና ለማሸነፍ ተጨማሪ ችሎታ ይኖረናል። በእዚህ ቅዱስ መሸሸጊያ፣ ሰላም እናገኛለን፤ እንታደሳለን እናም እንጠናከራለን። ”23

እንደገናም “ልብሽን አንሺ እናም ተደሰቺ፣ እና ከገባሽው ቃል ኪዳን ጋርም ተጣበቂ። ”24 ቃል ኪዳኖችን ማከበር እውነተኛ ደስታ ነው። ይህም መፅናኛና ሰላም ነው።

ከአለም ክፉዎችም መጠበቂያ ነው። ቃል ኪዳኖቻችንን ማክበር በፈተና ጊዜዎች ይረዳናል።

በክርስቶስ ስናምን እና ከቃል ኪዳኖቻችን ጋር ስንጣበቅ፣ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ የሚነገሮችን ደስታዎች እና በኋለኛ ቀን ነቢያት የተሰጡትን ተስፋ ቃላት እንቀበላለን።

ውድ እህቶች፣ አፈቅራችኋለሁ እና ይህን ታላቅ ደስታ በህይወታችሁ እንዲያጋጥማችሁ ተስፋዬ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።